የካልፎርኒያ ዩኒቨርስቲ በሎስ አንጀለስ

የጥናት ተሳታፊዎች

# የመብቶች ዝርዝር

የሚከተሉት በሕክምና ጥናት ውስጥ ለመሳተፍ ለሚጠይቅ ማንኛውም ግለሰብ ያሉትን መብቶች የሚያመለክቱ ሲሆኑ፤ እንደ አንድ ጥናት ውስጥ ተሳታፊ እኔ የሚቀጥሉት መብቶች አሉኝ፤፤

1. ጥናቱ ምን ለማግኘት እየሞከረ እንዳለ የማወቅ መብት አለኝ
2. ስለማናቸውም የጥናቱ ዘዴዎች፤ መድሃኒቶች፤ እና/ወይም መሳሪያዎች እና ማናቸውም ከተለምደው አሰራር እንዴት የተለዩ እንደሆኑ የማወቅ መብት አለኝ
3. በዚህ ጥናት ምክንያት ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ አደጋዎች፤ ጉድለቶች፤ ወይም ሊከሰቱ ስለሚችሉ ጉዳቶች የማወቅ መብት አለኝ
4. በመሳተፌ ይገባኛል የምላቸው ጥቅማ ጥቅሞች ምን እንደሆኑ የማወቅ መብት አለኝ
5. ስለአሉ ሌሎች አማራጮች እና እንዴት ጥናቱ ውስጥ በመሳተፌ የተሻሉ ወይም ያልተሻሉ እንደሆኑ የማወቅ መብት አለኝ
6. ጥናቱ ሌላ መዘዝ ቢያስከትል ምን አይነት ሕክምና ሊኖር እንደሚችለ የማወቅ መብት አለኝ
7. ጥናቱን ወይም ዘዴውን በሚመለከት ማንኛውንም አይነት ጥያቄ የመጠየቅ፤ እነዚህንም ጥያቄዎች ጥናቱ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ ጥናቱ እየተካሄደ በማንኛውም ጊዜ የመጠየቅ መብት አለኝ
8. በጥናቱ እስከጭራሹ አለመሳተፍም ሆነ ጥናቱ እየተካሄደ በማንኛውም ጊዜ የማቆም መብት አለኝ፤ ይህ ውሳኔዬም የማገኘውን እንክብካቤም ሆነ ከሐኪሜ ጋር ያለኝን ግንኙነት በማንኛውም መልኩ አያስተጓጉለውም
9. በጥናቱ ተመራማሪ የተፈረመና የተፈረመበትን ቀንም የሚያሳይ የፈቃድ ቅጽ ግልባጭ የማግኘት መብት አለኝ

10. በዚህ ጥናት ለመሳተፍ በምወስንበት ጊዜ ከማንኛቸውም ተጽእኖ ነጻ የመሆን መብት አለኝ

------------------------------------------------------

ማንኛቸውንም አይነት ጥያቄም ሆነ የሚያሳስበኝ ጉዳይ ካለ ተመራማሪውን ወየም ረዳቱን መጠየቅ እችላለሁ፤ ጥናት የሚካሄድባቸውን አካላት የሚከላከለውን ቢሮ (OHRPP) በተጨማሪም መገናኘት እችላለሁ፤ OHRPP በጥናት ተሳታፊዎችን የሚረዳ ድርጅት ሲሆን፤ ከሰኞ እስከ አርብ ከጥዋቱ 8 ሰዓት ጀምሮ እስከ 5 ከሰዓት በኋላ ድረስ መገናኘት እችላለሁ 310-825-5344, participants@research.ucla.edu በመደወል፤ ወደዚህ ቢሮ ሲደውሉ እንግሊዘኛም ሆነ ስፓኒሺኛ የማይችሉ ከሆነ የሚያስተረጉምልዎ ሰው እንዲገኝ መሆን ይኖርበታል፤ በተጨማሪም ለOHRPP መጻፍ በሚቀጥለው አድርሻ ይችላሉ፤
10889 Wilshire Blvd., Suite 830, Los Angeles, CA 90095-1406

05/2021